# <u>ወኔ ሲሸጋገር</u>

እኔስ መስሎኝ ነበር ተሟጠ ያለቀ
አሞቱ የፈሰሰ ወኔው የደቀቀ
ያድርባይነቱን የመስሎ ማደሩን ቀሚስ ያጠልቀ
ግራ ቀኝ ቀኝ ግራ ጀንበር በሰርቀ

ዘንድሮስ ተነስቷል ቆፍጣና ነኝ ብሏል
ታንኩን በጎራዴ ከረታው ተምሯል
ነፍጠኛ ላይ ወንጭፍ ድንጋዩን ወርውሯል
እስረኛም ሊያስመልጥ ግንዲላ ዘርግቷል

እምቢኝ አሻፈረኝ አልገዛም ብሎ
ፈሪን አንገዋሎ ድፍርሱን አጥሎ
ጨቋኝ ሊፈነግል ተገዝቶ ምሎ
ጀግኗል ዘንድሮስ ፈረሱን ኮልኩሎ

ልብ አርጎ ተነስቷል ተምሯል ካውልቱ
ከወደቁት ጀግኖች በየዘመናቱ
“ማን ይፈራል ሞት”ን ብለው ካለፉቱ
ፍቅር ነፍሳቸውን ላገር ከሰጡቱ

ዘንድሮስ ተምሯል ከዛ ጀግና ታጋይ
ከጅ አልሰጥም ባዩ ተስፋየ ደበሳይ
ከማርቆስ ከጋይም ካጥቂው ተከላካይ
ከነገለብ ዳፍላ ከነመምህር በላይ

እፎይ ተስፋ ዘራሁ ከትናንቱ ዛሬ
ይሰማ ጨኸቴ ይውጣ ተናግሬ
ዝም አልልምና ድምጼን ተጭበርብሬ
ሰሚ ጆሮ አግኝቼ ተተኪ ጀግናዎች እንደነሸብሬ

ታፈሰ ውብሸት